# የሀበሻው ዲፕሎማት ፍዳ (2)

ዘነበ ኃ/ማርያም ገነሜ

"*ማን ያውራ የነበረ ማን ያርዳ የቀበረ*" ነውና እኔም ዛሬ ከበረሃውና ከባህሩ የነፍስ አውጪኝ ሽሽት አድካሚ ጉዞ ድካም በኋላ ትንሽ አቅም ስላገኘሁ በደንብ ላጫውታችሁ:: ደግሞ ይህ ማን ነው? ምንስ ተነክቶ ነው? እንዳትሉ በአጭሩ ራሴን ላስተዋውቃችሁ:: ለነገሩማ ቀደም ሲል በዚሁ ድህረ ገፅ አንዲት አጠር ያለች መግቢያ ቢጤ አቅርቤ ነበር:: ነገር ግን የትግራይ ተወላጅ የወያኔ ካድሬዎችን ግፍና በደል ጠቃቀስኩና በርካታ ነገሮች በዕንጥልጥል መተዌ ስለተሰማኝ በድጋሚ ዘርዘር ባለ መልኩ ይህችን ላስነብባችሁ ወደድኩ::

እ.አ.አ 2007-2009 ስነዓ(የመን) በሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ በዲፕሎማት ደረጃ የተለያዩ የሥራ ዘርፎችን በኃላፊነት አከናውኛለሁ:: ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ኤምባሲው ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተመደብነው አንድ የሰነዓ ፎረም የወያኔ የፖለቲካ ሹመኛና ከሌላ ባለሙያ ዲፕሎማት ጋር ሦስት ሆነን ነው:: ይህ ባለሙያ ዲፕሎማትና እኔ አገራችንን ለማገልገል ከፍተኛ ተነሳሽነት ስለነበረን ከአላስፈላጊ የብሄር ፖለቲካ እንካ ሰላምታ ራሳችንን ቆጥበን የባለሙያ ሥራዎችን ብቻ አከናውነን ወደ ውድ ሀገራችን ለመመለስ ተመካከርን:: "የፈሩት ይደርሳል፤ የጠሉት ይወርሳል" እንዲሉ እኛም አልቀረልንም:: ወደ የመን ገብተን ጥቂት ወራቶችን እንኳን ሳናስቆጥር ከእኛው ጋር የተላከው ሹመተኛ ከመሰሎቹ ጋር ግንባር ገጥሞ ቁም ስቅላችንን ያሳየን ገባ:: መጀመሪያ አካባቢ በኤምባሲው ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የትግራይ ተወላጅና እነርሱ እንደሚሉት "ታጋዮች" መኖራቸው እኔንም ጓደኛዬንም ግርም ነበር ያለን:: ለማንኛውም ዝርዝራቸውንና የሚከፈላቸውን ደሞዝ እንዲሁም የተሰጣቸውን የዲፕሎማቲክ ደረጃ ልግለፅላችሁና እናንተው ፍረዱ::

ከአምባሳደሩ ልጀምርላችሁና ደሞዙ በአሜሪካን ዶላር 2500 (ሁለት ሺህ አምስት መቶ) ሲሆን ይህ ግለሰብ በአሁኑ ሥርዓት አገዛዝ አጠራር የሐረሪ ተወላጅ መሆኑን ይናገራል:: ግን ዓይመስለኝም ምክንያቱም ወያኔ የኦሮሞን ህዝብ ለማምታታትና ጨፍልቆ ለመግዛት የሚጠቀምበት የኦሮሞ ዲሞክራሲ ድርጅት (ኦህዲድ) አባል ነው:: ተወልዶ ያደገው አዲስ አበባ ሲሆን በምርጫ '97 ወቅት በዜሮ መሸነፉን ራሱ ነግሮኛል:: ግለሰቡ ብልጣብልጥ ሲሆን ገንዘብ ሲወድ ለጉድ ነው:: በአገር ላይ ከሚሰራ ግፍ መካከል አንድ ሚስጥር ላጫውታችሁ፣ ይህ ግለሰብ በተለይም ከኦማን፣ከፓኪስታንና ከኢራን እንዲሁም በየመን ከሚገኙ የግል ባለሀብቶች ጋር በመመሳጠር ዘመድ አዝማድ ሽርክና እንዲፈጥሩ አድርጓል:: በአሁኑ ወቅት አዲስ አበባ ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች ባዶ መሬቶችን ለአቅመ አዳም ባልደረሱ ልጆቹና በዘመድ አዝማድ ስሞች አስመዝግቦ አሳጥሮ ይገኛል:: አንድ እጅግ ዘመናዊ

ቤት በ9000 የአሜሪካን ዶላር (ዘጠኝ ሺህ) ለአንድ የአውሮፓ ሀገር ባለሥልጣን ማከራየቱን ነግሮኛል:: እንደ ሳይክል፣ በአረብ አገሮች የሚሰሩ ምንጣፎች፣ መጋረጃዎችና የመሳሰሉት ማከፋፈያ ሱቆች በመርካቶ እና በሌሎች አካባቢዎች እንዳለውም ነግሮኛል::

"አምባሳደር ይህንን እያነበብክ ከሆነ መቼም በቆይታህ ወቅት የነገርኩህ ውሸቱን ነው እንደማትለኝ አምናለሁ::" ይህንን የምናገረው የኢትዮጵያ ሚስጥር ሳይሆን የሆዳምነትና የስግብግብነት ሴራ ስለሆነ አንተና መሰሎችህ ከድርጊታችሁ ትንሽ ተቆጥባችሁ እነዚያ ምስኪኖች ረሃብንና ችግርን ለማሸነፍ አንተ ወደ ተወከልክበት ሀገር ለሚሰደዱ ኢትዮጵያውያን ድጋፍ ብታደርጉላቸው በሚል ነው:: በፍቅረ ነዋይ ከታወረው ህሊናቹ ተመልሳቹ ለእነዚያ ወጣት ሴት ኢትዮጵያውያን ሲደፈሩ፣ ገንዘባቸው ሲነጠቅ፣ ሲደበደቡ፣ በአሰቃቂ ሁኔታ ሲገደሉ እና አምሯቸውን ሲስቱ ጥብቅና ብትቆሙ በሚል ነው:: ሴት ልጆች እያሉህ ስለእነዚያ ምስኪን ችግረኛ ኢትዮጵያዊ ሴቶች ሲነሳብህ እንደማትወድ አውቃለሁ:: ለነገሩ አንተ በደም ተረማምዶ ሥልጣን የያዘ ሥርዓት ቅጥረኛ ስለሆንክ ሰብዓዊነት አይገባህም::

ሌላው በጣም የሚገርማችሁ የአደምኑር መሐመድ (በጦር ሜዳ ቅጥል ስሙ ወዲ ሃጂ) ነው:: በሥልጣን ኮነሬል በትምህርት ደረጃ ምንም:: ምን ማለትህ ነው ልትሉ ትችላላችሁ:: ነገር ግን እውነታው በሰነዓ የኢትዮጵያ ኤምባሲ 2700 የአሜሪካን ዶላር (ሁለት ሺህ ሰባት መቶ) -እንዲያውም ትንሽ ከፍ ይላል- ደሞዝ እየተከፈላቸው የሚገኙ ከማንበብና ከመፃፍ መዋጋት እንደሚቀል የሚናገሩ ደረጃው ኮነሬል የሆነ የትግራይ ተወላጅ (ታጋይ) አለ:: ለዚህ ግለሰብ ወያኔ በኢትዮጵያ ቤት ሰጥቶታል እንዲሁም የራሱ የሆነ ሌላ ቤት አለው:: በየመንም ቢሆን የቤቱን ኪራይና የመብራትና የስልክ (ሞባይል ጨምሮ) ፍጆታዎችን የሚከፍለው ወያኔ ነው:: ጃፓን ሰራሽ ዘመናዊ ላንድ ክሩዘር መኪና ተሰጥቶት ያሽከረክራል:: አደምኑር (ወዲ ሃጂ) ምንም ዓይነት ማስረጃ ሳያቀርብ ገንዘብ ማጥፋት እንዲችል ሙሉ ስልጣን አለው:: ይህ ግለሰብ ከሌሎች መሰሎቹ ጋር በመሆን መመሪያና ትዕዛዝ ለአምባሳደሩ ይሰጣል:: ምናልባት ይህን ፅሁፍ ግለሰቡ ካነበበ ወይም ካስነበበ አንድ ነገር ልበልና ወደ ሌሎቹ ልለፍ "እኔ ወደዚህ የመጣሁት ነገ የሚሆነው ስለማይታወቅ ይህቺን ገንዘብ ሰብስቤ ልጆቼ ተበትነው እንዳይቀሩ ይጠቅማቸዋል" እውነት ነው መሰለኝ:: "የአባትህ አገር ሲወረር አብረህ ውረር" ወይስ "አለማወቅ ያንገጫግጫል::" ምንም ይሁን ምን ግለሰቡ ወደ ኤምባሲው ሲላኩ የተነገራቸውን ዋነኛ ዓላማ ነው የገለፁት:: አንጃውን (የትግራይ ተወላጆችን) በኢኮኖም ማደራጀት:: በዚህ አይነት ሁኔታ ግለሰቦችን መጥቀምና ሀገርን መዝረፍ:: አጃይብ ነው እኮ እናንተዬ በዚህች አጭር የኤምባሲ ቆይታዬ ስንቱን ታዘብኩኝ መሰላችሁ:: በእውነት ነው የምላችሁ እነዚህ ወያኔዎች ጭፍራዎችንም ጨምሮ ለካ ዝርፊያ እያካሄዱ ነው:: 18 አመት ያህል አገሪቱ መከራዋን የምትበላው ለካስ የግለሰቦች ሆድ ብቻ እየተሞላ ነው::

ደግሞ የኢኮኖሚ እድገት ተመዘገበ የሚባለው በወያኔዎች መካከል የተጋበሰ ሃብት ብቻ ተሰልቶ መሆን አለበት:: ምክንያቱም የተሻለ ኢኮኖሚ ቢኖርማ አሁን በረሃብ የሚሞቱት ኢትዮጵያውያን ባልሞቱ ነበር:: አኮኖሚ እድገት ቢኖርማ ኖሮ ምስኪን ኢትዮጵያውያን በባህር ተሰድደው እኔ ወደ ነበርኩበት ድሃ አገር የመን ባልመጡ ነበር:: ዛሬም እኮ በአገሬ በረሃብ ከምሞት በየመን እስር ቤት ፍርፋሪ እየበላሁ እቀመጣለሁ ብሎ የመረጡ ኢትዮጵያዊያን ቁጥር የትየለሌ ነው:: ይህ የምነግራችሁ ልብ ወለድ ወይም ፖለቲካ ሳይሆን የኖርኩበትንና በዓይኔ ያየሁነትን ምስክርነት ነው::

ሌላው ግለሰብ በመግቢያዬ ላይ ከእኔና ከሞያ ባልደረባዬ ከሆነው እንዲሁም አንዳችን ለአንዳችን ብሶታችንን ከምንተነፍሰው ጓደኛዬ ጋር አብሮ ወደ ኤምባሲው የተመደበ ነው:: ስለጓደኛዬ ምን እንደደረሰበት በኋላ አወጋችኋለሁ:: አሁን ስለዚህ የትግራይ ተወላጅ ግለሰብ ልንገራችሁ:: የእንስሳት ሀኪም እንደነበር ይናገራል:: ጥርስ አገባኸው አትበሉኝና የእንስሳውን ባላውቅም በዲፕሎማሲው የሥራ ችሎታ የለውም:: በቆይታዬ ወቅት እንደነገረኝ ከሆነ ወያኔ ከደርግ ጋር ሲዋጋ ለትግራዩ አንጃ (ህወሓት) ገንዘብ በማሰባሰብ /fund raise/ ባደረገው አስተዋፅዎ በአንድ ዘመዱ አማካኝነት ተመልምሎ ነው ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የገባው:: ታዲያ እንዲህ አይነት ሰው ከሆነ ችሎታውን ከየት ያምጣው ልትሉኝ ይሆን:: ምን ለእነርሱ ምን ጉድ ይፈራሉ::

ትዝ ይላችሁ እንደሆነ ከምርጫ 97 ጋር በተያያዘ ፖለቲካ ተኮር ግምገማ በውጭ ጉዳይ ተደርጎ በርካታ ባለሙያዎች ተባረው ነበር:: መቼም በምትካቸው እንደገባው አልሰማንም እንዳትሉኝ:: በምርጫው ወቅት ከወያኔ ጎን ሆነው ሲያጫፍሩና ሲያሽቃብጡ የነበሩ ናቸው እኮ:: ባለሙያውማ ቦታ የለውም:: ሲናገር ደሞ አንተ ምንድን ነህ ነው የሚባለው:: ለማንኛውም ይህ ግለሰብ የሚያገኘው ደሞዝ 2994 የአሜሪካን ዶላር(ሁለት ሺህ ዘጠኝ መቶ ዘጠና አራት) ነው:: ደረጃው ሰነዓ ፎረም (የኢትዮጵያ-የየመንና የሱዳን የሦስትዮሽ መድረክ) ተሿሚ ነው:: አምባሳደሩን በቅርብ የሚከታተልና ቀጥታ መመሪያና ትዕዛዝ የሚሰጥ ነው:: ከስዩም መስፍን (የዓመታት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር) ጋር ዝምድና እንዳለው ነግሮኛል::

የኤምባሲውን የቆንስላ ክፍል የሚመራውና ደሞዙ 2800 የአሜሪካን ዶላር(ሁለት ሺህ ስምንት መቶ) የሆነ የትግራይ ተወላጅ የሆነው ጌታቸው ተፈሪ ነው:: ይህ ግለሰብ በኢሚግሬሽንና ዜጎች ጉዳይ ባለሥልጣን እንደነበረ ቀድሞ የሚያውቀው ሰው ነግሮኛል:: የጦር አዋጊና የወያኔ የአገር ቤት ቀንደኛ ሰላይ እንደነበረና በርካቶችን ለክፋት የዳረገ እንደሆነ አንድ የትግራይ ተወላጅ የቀድሞ የእነርሱ አባል የነበረ ነገር ግን ሥነ-ምግባር ችግር እንዳለበት ተገልፆ በእስር ከተቀጣ በኋላ ከሥራው መባረሩን የገለፀልኝ በባህር ወደ የመን የመጣ ግለሰብ ነው:: ለነገሩ የጌታቸው ክፋት አሁንም ቢሆን በውስጡ እንዳለ ያስታውቃል:: በኤምባሲው ስብሰባም ሆነ በተናጠል ውይይት እኔ ያልኩት ብቻ ተቀባይነት ካላገኘ ሞቼ እገኛለሁ

የሚል ነው። ለእኔ የተሰነሰረው ዛቻና ማስፈራራትማ ልነግራችሁ አልችልም። መጀመሪያ አካባቢ የግለሰቡ ችግር ይመስለኝ ነበር በኋላ ግን ሥርዓቱን የሚያራምዱት እንደዚህ ዓይነት ሰዎች መሆናቸውና የእንደኔ ዓይነት ሰው ደግሞ ሰርጎ ገብ ተደርጎ የሚወሰድ መሆኑን ተገነዘብኩ።

የመጨረሻውን ግለሰብ ማንነት ልግለፅላችሁና ወደ ዋናው አርዕስት ልግባ። በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ እና በሌሎች የአገሪቱ ክፍሎች ገዢውን ሥርዓት የሚቃወሙ ኢትዮጵያውያንን ማደኑንና ማሳደኑን እንደ ጀብዱ ነው የሚያወራው። ይህ የትግራይ ተወላጅ ላበረከተው አስተዋፅዖ ወደ እስራኤ፣ ደቡብ አፍሪካ እና ወደ ሌሎች አገሮች በሥራ ሰበብ ተልኳል። አሁን ደግሞ ይህው 2747 የአሜሪካን ዶላር (ሁለት ሺህ ሰባት መቶ አርባ ሰባት) እየተከፈለው አንደኛ ፀሐፊ ሆኖ አሁንም የደህንነት ሥራ ይሠራል። በየመን የሚገኙ ዜጎችን ከወያኔ በተመደበለት ገንዘብና ተሽከርካሪ(መኪና) ሌሎችን እየቀጠረና እየመለመለ በየመን የወያኔን ሥርዓት ለመቃወም የሚደራጁ ኢትዮጵያዊያንን እንዲሁም ለመደራጀት ያሰቡትን ለየመን የፖሊስና የፀጥታ ሰዎች ገንዘብ(ጉቦ) እየሰጠ እንዲበተኑ ያደርጋል። ግለሰቡ ከመጠን ያለፈ ትምክህተኛ ከመሆኑ የተነሳ በዚያ የሚገኙ ዜጎችን እንደሚያስገርፋቸው፣ እንደሚያሳስራቸው እና ወደ ኢትዮጵያ አሳፍኖ ማስወሰድ እንደሚችል ይናገራል።

አንድ ጊዜ ከዚህ ግለሰብ ጋር በባህር የመጡ ኢትዮጵያውያንን እኔ ለመመልከት እርሱ ደግሞ ቃለ-መጠይቅ እያደረገ ነጭ ወረቀት (ሊሴፓሴ) የሚሰራላቸውን ይወስናል። በወቅቱ የነበረው የአማራ ተወላጅ(አሁን በህይወት የለም) ምንም እንኳል የሥራው ኃላፊ ተደርጎ ቢወሰድም ትዕዛዝና መመሪያ የሚቀበለው ከዚህ ግለሰብ ነበር። አሁን የዚህ ዓይነቱ ውሳኔ የሚሰጠው ቀደም ብዬ በገለፅኩት ጌታቸው (ብሔር ትግራይ) በዚህ ግለሰብ አማካኝነት ነው። በእነርሱ አስተሳሰብ በባህር ተሰደው የሚመጡ ኢትዮጵያውያን በተለይ የኦሮሞና የአማራ ተወላጆች ከሆኑ ድብቅ የፖለቲካ አላማ እንዳላቸው ተደርጎ ነው የሚወሰደው። "ሌባ እናት ልጇን አታምንም" የሚባል ይህ ነው። እነርሱ በጎረቤት አገሮችና በየመን ተሰደው ነበር ያደረጉት። ዛሬ ሥራ ፍለጋ በአገሩ ተንከራትቶ ሳይሆንለት ወደ ባህር ማዶ ለህይወቱ ሳይሳሳ የተሰደደውን ምስኪን ወያኔ ላይ ለማሴር ነው በሚል መከራ ማሳየት ምን ይባላል።

የሚገርማችሁ ወያኔ ገና ለገና የጎረቤት አገሮች ለተቃዋሚ ቡድኖች መጠለያ ሰጥተው የትጥቅ ትግል ውስጥ እገባለሁ በሚል ፍራቻ ዜጎች እንደ ሱዳን፣ኬንያ፣ጅቡቲ፣የመን ባሉ አገሮች በደልና አስከፊ ጥቃት ሲፈፀምባቸው ምንም ዓይነት እርዳታ አያደርግም። ጥብቅና አይቆምም። አገሪቷን አዋረዷት። ለመሆኑ በርካታ የመኒዎች(የየመን ዜጎች) "ክብር ያላት ኢትዮጵያ በመንግሥቱ ጊዜ ቀረ" እንደሚሉ ታውቃላችሁ። ወያኔ እንደሚለው የዚያን ጊዜ ሥርዓት እያደነኩ አይደለም። እንዲያውም ታሪኩን ካልሆነ ብዙም አላውቀም። ታዲያ መች ይሆን ከዚህ ውርደትና ስደት የምንወጣው?

## ባይተዋርነት

ከላይ የጠቀስኳቸው ራሳቸውን "ታጋይ" ብለው የሚጠሩ የብሔረ ትግራይ ቡድን እኔንና ጓደኛዬን ግምገማ በሚል ሽፋን ቁም ስቅላችንን ያበሉን ጀመር፡፡ "ላም ባልዋለበት ..." ሆነና የእኔና የጓደኛዬ እጣ ፈንታ በእነዚህ ግለሰቦች ፊት ባይተዋር መሆን ነበር፡፡ አገርን ለማገልገል ባህር ተሻግረን በባዕድ አገር በጭንቅና በሰቀቀን መኖር ሆነ መጨረሻችን፡፡ ቀን እየገፋ በሄደ ቁጥር የእነዚህ ወያኔዎች ክፋት የበለጠ እየሰለጠነና እየበረታ መጣ፡፡ በሆነው ባለሆነው ውንጀላና ጥርጣሬ፣ ስድብና ግልምጫ ከልክ አለፈ፡፡ ጓደኛዬና የሥራ ባልደረባዬ አንድ ቀን በግምገማ ስም ስነልቦናው በመነካቱ ራሱን ስቶ ወደቀ፡፡ በኋላም ወደቤት ደግፌ ወሰድኩት፡፡ ረጅም ሰዓታት ራሱን ስቶ ቆየ፡፡ ነፍሱ መለስ ስትልለት "ዘኔ እዚህ ከምሞትብህ እባክህን ላስቸግርህ ወደ ሀገሬ እንድገባ አመቻችልኝ፡፡ በቃኝ ከእነዚህ ሰዎች ጋር፡፡" ነበር ያለኝ፡፡ እውነቱን ነበር፡፡ እኔም ያኔ እርሱን ብከተል ኖሮ በቀጣይ የደረሰብኝ የመከራ ገፈት ባልተቀበልኩ ነበር፡፡

እ.አ.አ ግንቦት 18 ቀን 2009 ረፈድፈድ ሲል ቶፊቅ አብዱላሂ (አምባሳደር) ደውሎ በአስቸኳይ እፈልግሃለሁ አለኝ፡፡ እኔም በፍጥነት ሄድኩኝ፡፡ ፊቱን ቅጭም አድርጓል፡፡ ደግሞ ምን ልባል ይሆን አልኩኝ በልቤ፡፡ በሩን ዘጋና እንድቀመጥ አዘዘኝ፡፡ አንተን አስምልክቶ ከአዲስ አበባ ብርቱ ሚስጢር መተላለፉን ነገረኝ፡፡ እውነቱን ለመናገር እጅግ በጣም ደንግጫለሁ፡፡ በኋላም ራሴን እንደምንም አረጋግቼ ሚስጢሩ ምን እንደሆነ ጠየኩ፡፡ በእጅህ የሚገኘውን ፓስፖርት አሁኑኑ አስረክብ ነበር ያለኝ፡፡ ጥያቄው ግልፅና ግልፅ ነበር፡፡ ስለዚህ ጥያቄዬ የነበረው በምን ወደ አገሬ ልመለስ ነው? ነበር፡፡ አምባሳደሩም ሌላ መፍትሄ ሊፈለግ እንደሚችል ነገር ግን አሁን የተሰጠው መመሪያ ፓስፖርቴ እንድሰጠው ግድ መሆኑን ገለፀልኝ፡፡ ይህንንም በአስቸኳይ ተፈፃሚ ካላደረኩኝ የየመንና የኢትዮጵያን መልካም የፖለቲካ ግንኙነት ተጠቅሞ እንደሚያስገድደኝ፣ በየመን ልሸሽግ ብል እንኳን አገሪቱ ልክ የኢትዮጵያ ክልል 5 (የሶማሌ) እንደሆነችና የትም ልገባ እንደማልችል ገለፀልኝ፡፡

እንዲሁም ለየመን የደህንነትና የፀጥታ አካላት በኢትዮጵያ መንግሥት እንደምፈለግ ዟሪ ደብዳቤ/ሰርኩላር/ ማሰራጨቱን ነገረኝ፡፡ እኔም በተቀመጥኩበት በድን ሆኜ ነበር፡፡ ይህ ለእኔ ይገባል ብዬ አስቤውም፣ አልሜውም አላውቅም፡፡ በፍፁም፡፡ ለካስ በባዕድ አገር እኔን መና ለማስቀረት በኤምባሲው ካድሬዎች ሲዶለትብኝ ከርሟል፡፡ "በሬ ካራጁ"፡፡ ዛሬስ ስንቶች ናችሁ ካራጃቹ ጋር ያላችሁ፡፡ ራሳችሁንና ያላችሁበትን ሁኔታ መፈተሹ ያዋጣችኋል፡፡

ያለኝ አማራጭ ማቄን ጨርቄን ሳልል በማንኛውም መንገድ ቢሆን ከዚያች ሀገር መሸሽ እንዳለብኝ ወሰንኩ፡፡ እንደ እብድ እጄን እያወራጨሁ መንገድ ለመንገድ ወዲያ ወዲህ ካልኩኝ በኋላ ወደ አንድ ጥግ ጥላ ስር ቆም አልኩኝና ለተወሰኑ

ደቂቃዎች ምን ማድረግ እንዳለብኝ አሰላሰልኩ። ሰማይ ሲደፋ ለማን ያዋዩታል። በኋላም የገዛ ጥላዬንም ቢሆን ማመን እንደሌለብኝ ወስኜ አለባበሴን ከቀየርኩ በኋላ በፔጆት መኪና ረጅም መንገድ ተጉዤ ወደ አንድ የየመን ክፍለ ግዛት ሌሊት ገባሁ። በዚያ ዓይነት ሆኔታ ሌትና ቀን የየመንን በረሃ አቋርጬ ከባህር ዳርቻ ደረስኩ። ምን ተስፋ አለኝ። እንባዬ በዝግታ ቢወርድም ከባህሩ የሚነፍሰው ነፋስ ጊዜ ሳይሰጥ ወዲያው ያደርቀዋል። ዓይኔ ተገዞ ያልጨረሰው የባህሩ ውሃ ተስፋ አስቆረጠኝ። ሌላ ትልቅ ባላንጣ ስለመሰለኝ ክፉኛ ጠላሁት። ደረቅ መሬት ቢሆን ምንም እንኳን ልምዱ ባይኖረኝም ከአሳዳጆቼ ለማምለጥ ራሴን እስክስት እጓዝ ነበር። ነገር ግን ፊቴ የተቆለለው የባህር ውሃን እንዴት አድርጌ ልሻገረው።

በዓይነ ህሊናዬ ከዜና አውታሮችና በሥራ ላይ የሰማኋቸው በሳሶ(ሶማሊያ) ወደ የመን የሚመጡ ኢትዮጵያውያን ታሪክ ትዝ አለኝ። እናም ሞትና መከራቸውን ሳስታውሰው ፍርሃት ተሰማኝ። ሆኖም ምን አማራጭ አለኝ። ስለዚህ ጀልባ ማፈላለግ ጀመርኩ። በኋላም በየመን ቆይታዬ ያዳበርኳትን መጠነኛ የአረብኛ ቋንቋ ተጠቅሜ ጀልባ ማፈላለጉን ቀጠልኩኝ። በኋላም ተሳካልኝ።

ከምሽቱ 2:00 ሰዓት አካባቢ ጀልባዋ ተንቀሳቀሰች። የባህሩ ሙቀት በደቂቃዊች ልዩነት እየጨመረ ነው። ጀልባዋ የብሱን በራቀች ቁጥር ጨለማው ድቅድቅ ከመሆኑ የተነሳ ዓይን ቢወጉ አይታይም። ከርቀት አልፎ አልፎ የሚታዩ ጭላንጭል መብራቶች አሉ። ሁሉም ነገር ፀጥ ረጭ ብሎ በጀልባዋ ሞተር የሚነፋረቀው የባህሩ ውሃ ብቻ ነው የሚሰማው። የእኔም አእምሮ አሁን ልክ እንደ አካባቢው ፀጥ ረጭ ብሏል። ምክንያቱም መዓበል ወይም የሆነ ነገር ቢፈጠር እንደምሞት አእምሮዬ ቀድሞ የተቀበለው መሰለኝ። ዋናም ደግሞ አልችልም። እኔና በባህሩ ላይ የተኛው ጨለማ እንደተፋጠጥን ሰዓታት አለፉ። አልፎ አልፎ ጀልባዋን የሚያወራጫት ጠንከር ያለ ነፋስ ሲነፍስ የዓይኔ ሽፋሽፍቶች ይርገበገባሉ። እኔ እንጃ ፍርሃት ወይም ድንጋጤ ሊሆን ይችላል። ለነገሩማ በድንም እኮ ይንቀሳቀሳል።

በድንገት በአእምሮዬ ውጭ ጉዳይ ያሳለፍኳቸውን ዓመታት ማሰላሰል ጀመርኩ። የመሥሪያ ቤቱ ሥራና አንዳንድ ግለሰቦች ትዝ አሉኝ። እረ ዲያ "ቢከፍቱት ተልባ" ብዬ በልቤ አእምሮዬ ልገታው ሞከርኩ። ግን አልተቻለኝም።